የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፭
አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 5
ADDIS ABABA 2nd December 2010

ደንብ ቁጥር ፩፻፺፪/፪ሺ፫
የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገፅ ፭ሺ፮፻፸፱

Regulation No. 192/2010
Sugar Corporation Establishment Council of Ministers Regulation ........................................Page 5679

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፪/፪ሺ፫

## የስኳር ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል::

**፩. አጭር ርእስ**

ይህ ደንብ "የስኳር ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፪/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. መቋቋም**

፩/ የስኳር ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል::

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል::

**፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል::

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 192 / 2010

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE SUGAR CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Sugar Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 192 / 2010".

**2. Establishment**

1/ The Sugar Corporation (hereinafter the "Corporation") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

**3. Supervising Authority**

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the Corporation.

ያንዱ ዋጋ Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

፭. **ዓላማ**

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ የሸንኮራ አገዳና ስኳር የሚያስገኙ ሌሎች ሰብሎችን ማልማት፤

፪/ ስኳር፣ የስኳር ውጤቶችን፣ የስኳር ተረፈ ምርቶችን እና የስኳር ተረፈ ምርት ውጤቶችን በፋብሪካ ማዘጋጀትና ማምረት፤

፫/ ምርቶቹንና ተረፈ ምርቶቹን ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ማቅረብ፤

፬/ አዳዲስና የማስፋፊያ የስኳር ልማት ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፣ የዲዛይን ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ መረጣና ድርድር፣ የተከላና ኮሚሽኒንግ ሥራዎች እንዲካሄዱ ማድረግ፤

፭/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሸንኮራ አገዳና በስኳር አመራረት ቴክኖሎጂ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ውጤቶችን በሥራ ላይ ማዋል፤

፮/ አቅሙ ካላቸው የሀገር ውስጥ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያስፈልጉ የማምረቻ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች ዲዛይንና ፋብሪኬሽን ሥራዎች በሀገር ውስጥ እንዲከናወኑ ማድረግ፤

፯/ በሕግ መሠረት ለሥራው የሚያስፈልገው መሬት ባለይዞታ መሆንና ማልማት፤

፰/ የአገዳ ምርታቸውን ለመንግሥት የስኳር ፋብሪካዎች የሚያቀርቡ አገዳ አብቃዮችን ማበረታታትና መደገፍ፤

፱/ ለስኳር ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠንና ጥራት ለማፍራት እንዲቻል ከሚመለከታቸው የትምህርት ተቋማት ጋር መተባበር፤

4. **Head Office**

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. **Purposes**

The purposes for which the Corporation is established are:

1/ to grow sugarcane and other sugar yielding crops;

2/ to process and produce sugar, sugar products, sugar by-products and products of sugar by-products;

3/ to sell its products and by-products in the domestic and export markets;

4/ to cause the undertaking of feasibility studies, design preparation, technology selection and negotiation, erection and commissioning of new sugar development and expansion projects;

5/ in cooperation with the relevant organs, to undertake studies and research in the field of sugar cane plantation and sugar production technologies and implement useful results thereof;

6/ in cooperation with capable domestic enterprises, to cause the designing and fabrication of machineries and spare parts required by public sugar factories;

7/ to possess, in accordance with the law, and develop lands required for its operations;

8/ to encourage and support sugar cane growers who are supplying their cane products to public sugar factories;

9/ to cooperate with the concerned educational institutions in producing the required type, number and quality of trained manpower for the sugar industry;

፲/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፲፩/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

፮. <u>ካፒታል</u>

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፵፩ ቢሊዮን ፱፻፺፱ ሚሊዮን ፯፻፴፩ሺ፪፻፷፬ (አርባ አንድ ቢሊዮን ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ስድሳ አራት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፮ ቢሊዮን ፵፪ ሚሊዮን ፭፻፲፪ ሺ ፮፻፲፬ (ስድስት ቢሊዮን አርባ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አሥራ ሁለት ሺ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

፰. <u>ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

፱. <u>የተሻሩ ደንቦች</u>

የሚከተሉት በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡-

፩/ የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፲፱፻፹፬፤

፪/ የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፹፬፤

፫/ የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፱/፲፱፻፹፮፤

፬/ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪)/፲፱፻፺፰ (እንደተሻሻለ)፡፡

10/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

11/ to engage in any other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. <u>Capital</u>

The authorized capital of the Corporation is Birr 41,999,731,264 (forty one billion nine hundred ninety nine million seven hundred thirty one thousand two hundred sixty four Birr) of which Birr 6,042,512,614 (six billion forty two million five hundred twelve thousand six hundred fourteen Birr) is paid up in cash and in kind.

7. <u>Liability</u>

The Corporation shall not be held liable beyond its total assets.

8. <u>Duration</u>

The Corporation is established for an indefinite duration.

9. <u>Repeal</u>

The following are hereby repealed:

1/ the Metahara Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 88/1992;

2/ the Wonji/Sheoa Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 89/1992;

3/ the Finchaa Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 199/1994;

4/ the Tendaho Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulation No. 122/2006 (as amended).

## ፲. <u>ስለኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መፍረስ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፭፻፬/፲፱፻፺፰ ተቋቋሞ የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፴፬ መሠረት በዚህ ደንብ ፈርሷል::

## 10. <u>Dissolution of the Ethiopian Sugar Development Agency</u>

The Ethiopian Sugar Development Agency established under Proclamation No. 504/2006 is hereby dissolved pursuant to Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

## ፲፩. <u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፰/፲፱፻፹፬ ተቋቁሞ የነበረው የመተሃራ ስኳር ፋብሪካ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፱/፲፱፻፹፬ ተቋቁሞ የነበረው የወንጂ/ሸዋ ስኳር ፋብሪካ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፱/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የፊንጫ ስኳር ፋብሪካ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፺፰ (እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ እና በአዋጅ ቁጥር ፭፻፬/፲፱፻፺፰ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ስኳር ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል::

## 11. <u>Transfer of Rights and Obligations</u>

The rights and obligations of the Metahara Sugar Factory established under the Council of Ministers Regulation No. 88/1992, the Wonji/Sheoa Sugar Factory established under the Council of Ministers Regulation No. 89/1992, the Finchaa Sugar Factory established under the Council of Ministers Regulation No. 199/1994, the Tendaho Sugar Factory established under the Council of Ministers Regulation No. 122/2006 and the Ethiopian Sugar Development Agency established under Proclamation No. 504/2006 are hereby transferred to the Corporation.

## ፲፪. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከጥቅምት ፲፱ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል::

## 12. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall come into force as of the 29th day of October, 2010.

አዲስ አበባ ህዳር ፳፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

Done at Addis Ababa, this 2nd day of December, 2010.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት